Government of South Australia

HomeStart FINANCE

Amharic 05/07

## ሆምስታርት ፋይናንስ

የራሳችሁን ቤት መግዛት ኣንድ ትልቅ ፍጻሜ ነው። ትክክለኛውን የቤት ብድር ማግኘት ግን፡ ኣስቸጋሪ (መቋቋም) ሊሆን ይችላል።

መክፈል በሚቻል የቤት ብድር ምክንያት፡ ሆምስታርት ብዙ ዓይነት ሰዎችን ረድቷል። ከመጀመርያ የቤት ገዢዎች እና ኣኗኗራቸውን ከፍ ለማድረግ ከሚፈልጉ ሰዎች እስከ በቤታቸው ላይ ዋጋ ለመጨመር ሊበደሩ ከሚፈልጉ ሰዎች ድረስ፡ ሆምስታርት፡ ለማንኛውም ሰው ሊስማማ በሚችል የቤት ብድር ሊያቀድ ይችላል።

የርስዎ ሁኔታ ምንም ቢሆን፡ የቤት ባለቤትነት የመሆን ሕልምዎ ለመሳካት እንዲችል፡ ትክክለኛውን ፋች ለማግኘት እንዲረዳዎ፡ ሆምስታርት እዚህ ኣለ (ይገኛል)።

## ለምንድነው ሆምስታርትን መምረጥ ያለብኝ?

ሆምስታርት ከዚህ በታች በሚከተሉት ጥቅሞች ያቀርብሎዎታል፡

- የክፍያ ደሕንነት – ከወለድ መጠኖች ጋር ያልተያያዙ፡ እና ኣብዛኛውን ጊዜ፡ ባጠቃላይ ዋጋ መናር ላይ የተመሠረቱ፡ ባመት ኣንዴ ብቻ የሚጨምሩ፡ የማያሳስቡ (ከመጨነቅ ነጻ የሆኑ) የብድር ክፍያዎች የመኖር
- ያበዳሪዎች የንብረት ዋስ የኢንሹራንስ ክፍያ የሌለበት – ለወደፊት በሺ የሚቀጠሩ ገንዘቦች ለመቆጠብ የሚያስችላቹህ
- በብድር እርዳታ ለተደረገላቸው፡ ኣነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች፡ 'የመጨመር' ኣማራጮች የመኖር
- በስልክ ግላዊ የሆነ የብድር ተመን የማቅረብ።
- ከመሳብ ጋር ብድሮች፣ የክፍያ መተጣጠፍ፣ ቋሚ ኣለመሆን፣ ቋሚ እና ክፍልፋይ ያራጣ ዋጋዎች፣ እና ቋሚ ኣራጣ ያልያዙ ንብረቶች (ድርሻዎች) ምርጫዎች የመኖር

## እኔ የሆምስታርት ብድር  ለማግኘት ብቁ ነኝ ወይ?

ለሆምስታርት ብድር ብቁ ለመሆን፡

- የተለመደ ገቢ መኖር ኣለበት – (ይህ የሴንተርሊንክን ክፍያዎች ያጠቃለለ ነው)
- ዕድሜ ከ18 ዓመታት በላይ መሆን ኣለበት
- የኣውስትራልያ ቋሚ ተቀማጭ ወይም ዜግነት መኖር ኣለበት
- በገዛችሁት ቤት ለመኖር ያሰባቹህ መሆን ኣለባቹህ
- ቤትዎን በደቡብ ኣውስትራልያ ውስጥ መግዛት ኣለብዎት

## ኣስጀምሩኝ

የሚያስፈልገዎትን ለመነጋገር፣ ወይም የርስዎን ብድር ከማጽደቅ በፊት ያለውን ሥራ ለመጀመር፡ ሆምስታርትን በስልክ ቁጥር (08) 8203 4000 ወይም ከከተማ ውጭ፡ በነጻ መደወያ ቁጥር 1800 018 788 በማድረግ ለሆምስታርት ይደወሉ።

መምዘኛው፡ ስምምነት፣ ሁኔታዎችን እና ብቃትን የሚያሟላ ነው። ዋጋ እና ክፍሊቶች ተከፋዮች ናቸው።